# የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በመጋቢትና ሚያዝያ ወራት የወሰዳቸው ወታደራዊ እርምጃዎች አጠቃላይ ሪፖርት

የኦሮሞ ህዝብ ጋሻና መከታ የሆነው ጀግናው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (ኦነሰ) ባለፉት ሁለት ወራት ማለትም በመጋቢትና ሚያዝያ በተለያዩ የኦሮምያ አካባቢዎች በጠላት ሃይል ላይ የሚወስዳቸውን ወታደራዊ እርምጃዎች አጠናክሮ ቀጥሏል። በእርምጃዎቹም ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦችና የፖለቲካ ካድሬዎች የሚገኙባቸውን ጨምሮ ከጠላት ሃይል በብዙ ደርዘኖች የሚቆጠሩትን ሙትና ቁስለኛ ሲያደርግ በርካታ ከባድና ቀላል የጦር መሳሪያዎችን በመማረክ የነጻነት ትግሉ ንብረት አድርጎአል። ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ሌሎች ጠላት ሲገለገልባቸው የነበረ የጦርና ሎጂስቲክ መሳሪያዎችን ደምስሷል። አንድ የወያኔ ወታደራዊ ካምፕም ሙሉ በሙሉ ሲደመሰስ አንድ ሰላማዊ ነዋሪ በሃሰት ተወንጅሎ የሚታሰርበት የገጠር ፖሊስ ጣቢያ ደግሞ በከፊል ተቃጥሏል። ከዚህም በተጨማሪ ኦነሰ እነዚህን ወታደራዊ እርምጃዎችን በወሰደባቸው ወቅት አንዳንድ የገጠር ከተሞችን ለቀናት ያህል ተቆጣጥሮ በመቆየት የድርጅቱን ባንዲራ ሰቅሎ ለነዋሪው ህዝብ አስፈላጊውን የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ማጎልበቻ ትምህርት ሰጥቷል። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ወታደራዊ እርምጃዎቹን የት የትና መቼ እንደወሰዳቸው ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ተገልጿል።

## መጋቢት 1 ቀን 2013- ምእራብ ሀረርጌ

በምስራቅ ኦሮምያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል ሙሉ በተሰኘች ከተማ ውስጥ በሚገኘው የሚሊሻ ጽህፈት ቤት ላይ ከሌሊቱ 8 ሰአት ገደማ ጥቃት አደረሰ። በዚጥ ጥቃት 6 ክላሺንኮቭ ጠመንጃዎችና ከ20,000 በላይ የሚሆኑ ጥይቶችን በመማረክ የነጻነት ትግሉ ንብረት አድርጎአል። ጽህፈት ቤቱን ሲጠብቁ የነበሩና ስማቸው አህመድ ጋብ እና አዳዌ ጃማ ኢዶ የተባለ የሚሊሻ አባላት በዚሁ እርምጃ ወቅት ተማርከው በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ቁጥጥር ስር ውለዋል።

## መጋቢት 2 ቀን 2013- ምስራቅ ወለጋ

በምእራብ ኦሮምያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በተጠቀሰው እለት በኢንቨስተርነት ስም በዞኑ ውስጥ እየተዘዋወረ ሰላማዊ ዜጎችን በሃሰት ወንጅሎ ሲያሳስር በቆየ አንድ የወያኔ ሰላይ ላይ የማያዳግም እርምጃ ወስዷል። ምትኩ አጽብሃ የተባለውና በኢንቨስተርነት ሽፋን የወያኔ ቅጥረኛ ሆኖ ህዝብን በማዋከብና መሬት በመዝረፍ ስራ ላይ የተሰማራው ይህ ወንጀለኛ በጊዳ ኣያና እና በጉቶ ጊዳ ወረዳዎች መካከል እየተመላለሰ ለወያኔ ሲሰራ የቆየ ሲሆን በተጠቀሰው እለት በአንገር ወንዝ አቅራቢያ በተወሰደበት እርምጃ ተገድሏል።

## መጋቢት 6 ቀን 2013- ምስራቅ ወለጋ

በዚህ እለት በዞኑ የጊዳ ወረዳ ጉቲን ከተማ ንብረትነቱ የሁለት የወያኔ ካድሬዎች የሆነ አንድ የነዳጅ ማደያ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት እርምጃ ተደምስሷል። የነዳጅ ማደያው ባለቤት የሆኑት ተስፋዬ ከበደና ሁሪ አለማየሁ የተባሉት የወያኔ ካድሬዎች የአካባቢውን ሰላማዊ ነዋሪዎች በኦነግ ደጋፊነት እየወነጀሉ በማሳሰር የሚታወቁ ሲሆን ከዚህ አኩይ ድርጊታቸው እንዲመለሱ በተደጋጋሚ ተመክረው ሊታረሙ ባለመቻላቸው በንብረታቸው ላይ እርምጃ መወሰዱን የዞኑ የኦነሰ እዝ አስታውቆአል።

## መጋቢት 9 ቀን 2013- ምስራቅ ወለጋ

የወያኔ ሃይሎች ተጎራባች የሆኑትን የጉሙዝ ብሄረሰብ አባላትን አስታጥቀው ኦሮሞን ለማስመታት ብሎም በሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች መካከል ግጭት ለመጫር እየጣሩ መሆናቸውን አስቀድሞ የተረዳው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በጸብ አጫሪው የወያኔ ሃይል ላይ እርምጃ ወሰደ። በዚህም እርምጃ ጠላት ሲጠቀምበት የቆየውንና 28 ጎጆዎች ያሉበትን አንድ ወታደራዊ ካምፕ መሉ በሙሉ ደምስሷል። በእርምጃው የተደናገጠው የወያኔ ሃይል እልኩን ለመወጣት ሲል ጦሩን ከነቀምቴ ከተማ ወደ ስፍራው ለመጫን ጥረት ቢያደርግም የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት አቡዬኮ በተቶ በተባለ ስፍራ አስቀድሞ መንገድ በመዝጋቱ የጠላት ጦር የሁዋልዮሽ ለመመለስ መገደዱ ተረጋግጧል።

በዚሁ በተጠቀሰው እለት የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በምስራቅ ወለጋ ዞን ሃሮ ሊሙ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መካከል ልዩ ስሙ ገባ ኢያኒ በተባለ ስፍራ በወሰደው እርምጃ ሁለት የወያኔ ቀንደኛ ካድሬዎችን በሞት ሲቀጣ ሶስቱን ደግሞ አቁስሏል። በእርምጃው የተገደሉት ሁለቱ የወያኔ ካድሬዎች ዳንኤል ስዩም እና አሰፋ ገ/ጽዮን የተባሉ ሲሆን የቆሰሉት ሶስቱ ደግሞ ታዬ አበበ፣ ኢራርሳ አምሳሉ እና ታደለ ገበየሁ የተባሉት መሆናቸው ተለይቷል። ካድሬዎቹ ይንቀሳቀሱበት የነበረው ታርጋ ቁጥሩ ኢ.ኢ.05726 የሆነ ተሽከርካሪም በዚሁ እርምጃ ወቅት ተደምስሷል።

መጋቢት 14 ቀን 2013- ፊንፊኔ

በማእከላዊ ኦሮምያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ሪሳ (ነስር) በመባል የሚታወቀው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ጠንካራ ክንፍ በተጠቀሰው እለት ከምሽቱ 2 ሰአት ተኩል ላይ በፊንፊኔ ቦሌ ክፍለ ከተማ ጨፌ ኮንዶሚኒዬም እየተባለ በሚጠራው ሰፈር በወሰደው የደፈጣ እርምጃ ነዋሪውን ህዝብ በሃሰት በመወንጀልና በማዋከብ የሚታወቁ 3 የስርኣቱ ቅጥረኞችን ሲገድል 8ቱን ደግሞ አቁስሏል። በዚህ እርምጃ የተደናገጠው የወያኔ ስርኣት መያዣ መጨበጫ ጠፍቶት ሰላማዊ ህዝብን ማሸበር መያያዙን ለማወቅ ተችሏል።

መጋቢት 14 ቀን 2013- ሰሜን ሸዋ

በዚህ እለት ከምሽቱ 5 ሰአት ገደማ ላይ በጂዳ ወረዳ ሲርጢ በተባለች ከተማ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ሪሳ ክንፍ በወሰደው ጥቃት ሁለት የወያኔ ፖሊስ አባላትና ኤሊያስ ቶልቻ የተባለ አንድ የከተማዋን የመንግስት ካድሬ በሞት ቀጥቷል። ሶስቱ ግለሰቦች በአካባቢው ለዘመናት ነዋሪውን ህዝብ ሲያስፈራሩና በሃሰት እየወነጀሉ ሲያሳስሩ የኖሩ ሲሆን ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ተመክረው አሻፈረኝ ያሉ መሆናቸው ተረጋግጧል።

መጋቢት 25 ቀን 2013- ምስራቅ ወለጋ

በዚህ ዞን በሳሲጋ ወረዳ ልዩ ስሙ ሶጌ በተባለ ስፍራ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በተጠቀሰው እለት በወሰደው እርምጃ የአካባቢውን ሰላማዊ ህዝብ በማዋከብ የሚታወቁትን ሁለት የወያኔ ታጣቂዎችን ሲገድል አንዱን ደግሞ አቁስሏል። በሞት የተቀጡት ሁለቱ ታጣቂዎች ከፍያለው ታደለና ኢያሌው አበባው የተባሉ ሲሆን በአርምጃው የቆሰለው ደግሞ መኮንን የተባለ የወያኔ ታጣቂ መሆናቸው ታውቆኣል።

ሚያዝያ 4 ቀን 2013- ምስራቅ ወለጋ

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በዞኑ ሃሮ ሊሙና ያሶ በተባሉ ወረዳዎች መካከል ልዩ ስሙ ሉጎ ቦቃ በተሰኘ ስፍራ በወሰደው የደፈጣ ጥቃት የሰሌዳ ቁጥሩ ኦሮ01286 በሆነ ፓትሮል መኪና ተጭነው ለአሰሳ ተግባር ይንቀሳቀሱ የነበሩ የወያኔ አሸባሪ ታጣቂዎችን ሙትና ቁስለኛ አድርጎኣል። በጥቃቱ 2 የጠላት ታጣቂዎች ወዲያው ሲገደሉ 4ቱ ደግሞ

በጽኑ ቆስለዋል። ሲንቀሳቀሱበት የነበረው ተሽከርካሪም በደረሰበት ጥቃት ከጥቅም ውጭ ተደርጎአል። በጥቃቱ የተገደሉት ሁለቱ የወያኔ ታጣቂዎች ደመላሽ ኣታኽልቲ እና ፍሰሃዬ ወ/ስላሴ የሚባሉ ሲሆን የቆሰሉት ደግሞ ስማቸው ለጊዜው አልታወቀም።

ሚያዝያ 5 ቀን 2013- ምእራብ ሀረርጌ

በዚህ እለት በዞኑ የሚኤሶ ወረዳ ልዩ ስሙ ቡሪ ቱምቱ በተባለ ስፍራ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በጠላት ጦር ላይ በወሰደው የደፈጣ ትቃት 3ቱን ወዲያው ሲገድል 5ቱን በጽኑ ኣቁስሏል።

ሚያዝያ 8 ቀን 2013- ምስራቅ ሀረርጌ

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በሙዩ ሙሉቄ ወረዳ የምትገኘውንና ሁሴ ተብላ የምትጠራ የገጠር ከተማ ሙሉ በሙሉ ከሚያዝያ 8 ቀን ጀምሮ ለኣንድ ሳምንት ያህል ተቆጣጥሮ ቆይቷል። በዚህ ወቅት ለከተማዋና ኣካባቢዋ ነዋሪዎች ኣስፈላጊውን የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ማዳበሪያ ትምህርት የሰጠ ሲሆን ከሳምንት ቆይታ በሁዋላ ከተማዋን በገዛ ፈቃዱ ለጊዜው በመልቀቅ ለቀጣይ እርምጃ ወደ ሌላ ስፍራ ተንቀሳቅሷል።

ሚያዝያ 17 ቀን 2013- ምእራብ ሀረርጌ

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በዚህ እለት በምእራብ ሀረርጌ ልዩ ስሙ ጉጂ በተባለ ስፍራ በሰፈረው የወያኔ ጦር ላይ በወሰደው የደፈጣ ጥቃት 7ቱን ወዲያው ሲገድል 5ቱን በፅኑ ኣቁስሏል። በዚሁ እለት በዞኑ የሚኤሶ ወረዳ ኣሰቦት ከተማ የኣካባቢውን ነዋሪ ዜጎችን በሃሰት እየወነጀለ ሲያሳስር የቆየ ራህሙቶ በመባል በሚጠራ የወያኔ ጀሌ ላይ የግድያ እርምጃ ወስዷል።

ሚያዝያ 20 ቀን 2013- ምስራቅ ወለጋ

በሃሮ ሊሙ ወረዳ ልዩ ስሙ ሱጌ በተባለ ኣካባቢ በሚገኝና ለሰላማዊ ዜጎች ማጎሪያነት የተቋዋቋዋመውን የወረዳዋን ሁለተኛው የፖሊስ ጣቢያ በመክበብ ባደረሰው ጥቃት የፖሊስ ጣቢያውን በከፊል የደመሰሰ ሲሆን መልካሙ የተባለው የፖሊስ ኣባልም በዚሁ እርምጃ ወቅት በጽኑ መቁሰሉ ታውቆኣል።

ሚያዝያ 21-22 ቀን 2013- ሰሜን ሸዋ

በተጠቀሱት ሁለቱ ተከታታይ ቀናት በሰሜን ሸዋ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ጀግናው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ራሳ ክንፍ ኣንድ መቶ ኣለቃና ኣንድ ሃምሳ ኣለቃ የሚገኙባቸውን ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችን ጨምሮ 12 የጠላት ጦር ኣባላትን ሲገድል ቁጥራቸው ከዚህ የሚልቁትን ደግሞ በጽኑ ኣቁስላል። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ሚያዝያ 21 ቀን በዞኑ የደገም ወረዳ ቁርቁራ በተባለች ከተማ በሰፈረው የወያኔ ሃይል ላይ ባደረሰው ጥቃት 7ቱን ወዲያው ሲገድል ሌሎችን ደግሞ ኣቁስሏል። ከተገደሉት መካከል ሲሳይ ሃብቴ የተባለ ሃምሳ ኣለቃ፣ ዘውገ ወርቁ የተባለ ኣስር ኣለቃ፣ እንዲሁም ሃይሉ ደሳለኝ፣ ጌቱ ዘውዴ እና ኣፈወርቅ ወ/ማሪያም የተባሉ ለጊዜው ማእረጋቸው ያልታወቀ ወታደራዊ መኮንኖች ይገኙባቸዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ሚያዝያ 22 ቀን 2013 በሰሜን ሸዋ ጀማ ወንዝ ኣቅራቢያ ልዩ ስሙ ስልሚ በተባለ ስፍራ በወሰደው የደፈጣ ትቃት በቀለ ደምሴ የተባለ የመቶ ኣለቃን ጨምሮ 4 የስርኣቱን የጦር ኣባላት ገድሏል። የኣካባቢው ነዋሪ ህዝብ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በጠላት ሃይል ላይ በተደቀዳጀው ድል እጅግ በመደሰት የትግል ቁርጠኝነቱን ይበልጥ በማጠናከር ከኦነግ ጎን መሰለፉን መግለጹንም የኦነሰ ሰሜን እዝ ኣስታውቆኣል።

ሚያዝያ 25 ቀን ሀ013- ምእራብ ሀረርጌ

በምስራቅ ኦሮምያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ኦነሰ በጠላት ሃይል ላይ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ኣጠናክሮ በመቀጠል በተጠቀሰው እለት ሙሉ እና ሚኤሶ በተባሉት ከተሞች መካከል በምትገኘውና ልዩ ስሟ ጭቂርቲ በተባለች ስፍራ የኦሮሞ ተወላጆችን ትጥቅ ለማስፈታት በተሰማራ የወያኔ ጦር ላይ ተኩስ ከፍቶ ኣንዱን ወዲያው ሲገድል ሌሎቹን በማቁሰል የጠላትን ዘመቻ ኣላማ ማምከኑን የዞኑ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት እዝ ኣስታውቆኣል።

የኦሮሞ ህዝብ ጋሻና መከታ የሆነው ጀግናው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ወደተለያዩ የኦሮምያ ዞኖች የሚያደርገውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ በማስፋት በወያኔ ሃይል ላይ የሚወስደውን እርምጃ ይበልጥ ኣጠናክሮ እንደሚቀጥል የሰራዊቱ ጠቅላይ እዝ ኣስታውቆኣል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!